# የኢትዮጵያን ሉዓላዊነት ለማስከበርና የግንቦት 1997ን ዕልቂት ለመዘከር የሚደረግ ሰላማዊ ሠልፍ!

የእናትና አባቶቻችን አጥንት ተከስክሶ፤ ደማቸው ፈስሶ፤ የህይወት መስዕትነት ተከፍሎበትና በዚህም ተከብሮ የኖረው የኢትዮጵያ ዳር-ድንበር፤ ዛሬ በህወሃት/ኢሕአዴግ አሳፋሪና በታሪክም ምህረት የማይደረግለት ትብብር በሱዳን ወራሪ ወታደሮች ተደፍሯል። ከሰሜን እስከ ደቡብ (ጎንደር፣ ጎጃም፣ ወለጋና ኢሉባቦር) ባለው አዋሳኝ የሚኖረው ወገናችን፤ አሁንም እንደጥንቱ ተጋዳይ አርበኛ አባቶቻችን ሁሉ የአገሩን ዳር ድንበር ላለማስደፈር ከሱዳን ጦር ጋር ጉሮሮ ለጉሮሮ እየተናነቀ በመዋደቅ ላይ ይገኛል።

ግንቦት ላይ ሆነን ግንቦት 1997 (2005)ን በዓይነ-ህሊናችን ስንቃኝ ደግሞ ለኢትዮጵያ ፍትኅና ዴሞክራሲ ለማምጣት ሲታገሉ የወደቁትን ሰማዕታት እናስታውሳለን። ምንም እንኳ በህዝባችን መሃል ተገኝተን የመከራው ገፈት ተቋዳሽ ባንሆንም፤ በስደት የምንገኘው እኛ ወገኖቹ ግን ከጎኑ በመቆም ለዚህ አገሩንና ክብሩን ለማስጠበቅ ቆርጦ ለተነሳውና እየተዋደቀም ላለው ወገናችን ቢያንስ አጋርነታችንንና ድጋፋችንን ልናረጋግጥለት ይገባል። ስለዚህም እኛ በቶሮንቶ፤ በኦታዋና በሞንትሪያል የምንኖር ኢትዮጵያውያን በአንድነት ስሜትና በቁጥር ብዛት ወጥተን ከቆራጥ እናት-አባቶቻችን፤ ወንድሞቻችንና እህቶቻችን እንዲሁም የወደቁት ሰማዕታት ከተሰውለት ዓላማ ጎን በመሠለፍ፤

1) ወራሪው የሱዳን ጦር ልቡን፤ ዓይኑንና እጁን ከኢትዮጵያ ላይ እንዲያነሳ ሰላም ወዳድ የሆኑ የዓለም መንግሥታትን፤ የካናዳን መንግሥትና ህዝብ እንዲሁም ዲፕሎማቶችና የሰብዓዊ መብት ድርጅቶችን ለመማጸን፤
2) ለኢትዮጵያ ፍትኅ ለማምጣት በምርጫ 97 እንዲሁም ከዚያም በፊትና በኋላ ሲታገሉ የወደቁትን ወገኖቻችንን አስቦ ለመዋል ሰላማዊ ሠልፍ ጠርተናል።

ስለዚህም የምትችሉ ኢትዮጵያውያን ሁሉ በቦታው እንድትገኙልን
በታላቅ ትህትና እየጠየቅን፤

**ሠልፉ የሚደረግበት ከተማም፡** ኦታዋ (ካናዳ)

**ቀኑ፡** ግንቦት 15፤ 2000 ዓ/ም (May 23, 2008)

**ሰዓቱ፡** ከቀኑ 7 ሰዓት (1:00PM) ጀምሮ

**የሠልፉ መነሻ ቦታ፡** ከኦታዋ ማዘጋጃ ቤት ፊት ለፊት የሚገኘው የህዝብ መናፈሻ

ስለሠልፉ ዝርዝር ጉዞም በመነሻው ቦታ መግለጫ ይሰጣል።

ለተጨማሪ መረጃ በስልክ ቁጥር፡ (416) 824-7858 ወይም (613) 867-9292 ይገናኙን

**የሠልፉ አዘጋጅ ኮሚቴ (ቶሮንቶ፤ኦታዋ፤ሞንትሪያል)**